# የአቶ ስዬ መድኅንነትና ፖሊቲከኛነት

*መስፍን ወልደ ማርያም*

*ታኅሣሥ* 2002

በሁለት መሠረታዊ ቁም-ነገሮች ላይ አተኩራለሁ፤ አንደኛው ቁም-ነገር አቶ ስዬ የአንድነትን ፕሮገራም ማስለወጡ ነው፤ ሁለተኛው አቶ ስዬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ ለመስጠት የሚያስችለው ደረጃ ላይ አልደረሰም ማለቱ ነው፤ ለየብቻቸው ጠጋ ብለን እንያቸው፡፡

**አንደኛ የአንድነት ፓርቲ ፕሮገራምን ማስለወጡ**፤ እጅ መንሻም ይሁን ማባበያ ባይታወቅም አንድነት ከተመሠረተ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ ግብዣ በግዮን ሆቴል ተደግሶ ዶር. ነጋሦና አቶ ስዬ የአንድነት ፓርቲ አባሎች እንዲሆኑ የተጠየቁ ይመስላል፤ የአቶ ስዬም መልስ በዕለቱ ባደረገው ንግግር ተገልጾአል፤ እንደተናገረው የአንድነት ፕሮግራም በጠቅላላ ጉባኤው እሱ እንደሚፈልገው ሆኖ መለወጥ አለበት፤ የአንድነት አባል የሚሆነው ይህ ከተፈጸመ ብቻ ነው፤ አንድ ሰው የአንድ ፓርቲን ፕሮግራም ለውጡና አባል እሆናለሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?

እስቲ በምናውቀውና ባህላችን በሆነው ማኅበር እንመልከተው፤ ሰዎች ተሰብስበው አንድ የሚፈልጉትን መልአክ ወይም ሰማዕት ወይም ጻድቅ ወይም የአምላክን ስም መርጠው፣ አንድ ሙሴ ሰይመው ማኅበር ይጠጣሉ፤ ለምሳሌ የገብርኤል ማኅበር ነው እንበል፤ አቶ ስዬ ወይም ሌላ ሰው መጥቶ ከደካማው ሙሴ ጋር ተነጋግሮ ማኅበሩ የገብርኤል በመሆን ፋንታ የሚካኤል አድርጉትና እኔም አባል እሆናለሁ ቢል ምን ማለት ነው? ለእኔ እንደሚታየኝ፣

- አቶ ስዬ ወይም ሌላ ጥያቄውን የሚያቀርብ ሰው ባልታወቀ ሚዛን ማኅበሩን ከመሠረቱት ሰዎች እኔ እበልጣለሁ፤ የእኔ ፍላጎት ከእነሱ ፍላጎት ይበልጣል፤ ማለቱ ነው፤
- ሚካኤል ከገብርኤል እንደሚሻል አውቃለሁና የምነግራችሁን ተቀበሉ ማለቱ ነው፤
- በመጨረሻም የእኔ እምነት ከእናንተ እምነት ይበልጣል፤ የእኔ እውቀት ከእናንተ እውቀት ይበልጣል ማለቱ ነው፤
- ተንኮል ለሚታየው ሰው ደግሞ ስንት የሚካኤል ማኅበር እያለለት፣ ወይም እሱ አዲስ የሚካኤልን ማኅበር ለመመሥረት የተቸገረበትና የገብርኤልን ማኅበር ለማፍረስ የመረጠበት ምክንያት ጤናማ መስሎ አይታየውም ይሆናል፤

ለማናቸውም አቶ ስዬ ደካማ ሙሴ አገኘና የአንድነት ፓርቲን ዋናና መለያ የሆኑትን የፕሮግራም ክፍሎች እንዲሰረዙና እሱ በሚፈልጋቸው እንዲተኩ ለማድረግ ቻለ፤ ገብርኤል በሚካኤል እንደተተካው! ይህ ፖሊቲካ (ያውም አጉል ፖሊቲካ) ሊባል የሚቻለው ሙሴውና አቶ ስዬ አንድነትን ለማፍረስ ተስማምተው ከሆነ ብቻ ነው፤ ነገር ግን የአንድነት መፍረስ ማንን ያሳድጋል? የአንድነት መሪ ነኝ የሚለው ኤንጂኒር ግዛቸው (ሙሴ) ልጅ አክሎግ ለመንህን ከአሜሪካ፣ የአሜሪካንና የጀርመን ራድዮኖችን፣ አንዳንድ ጋዜጦችን፣ የአሜሪካን፣ የብሪታንያንና የጀርመን ኤምባሲዎችን ይዞ (በኤንጂኒር ኃይሉ ሻውል አባባል ለመጠቀም) ‹‹እየተኮረኮመ›› ቁም ነገርን በጥቅም

በመለወጥ አንድነትን የማፍረስ ተልእኮውን እየፈጸመ ነው፤ የሚያዛልቅና የሚያኮራ ሥራ አይደለም።

ከዚህ ሁሉ የምንደርስበት መደምደሚያ ምንድን ነው? ግልጹ መደምደሚያ ጫካ ወይም የትጥቅ ትግል የፖሊቲካ ልምድ አይሆንም፤ በጡንቻ የራስን ፈቃድ በሌሎች ላይ መጫንን እንደዋና መመሪያ አድርጎ መጠቀም ባህል ይሆናል፤ ፖሊቲካ የሕዝብን ስሜት፣ አስተሳሰብና ፍላጎት ለመረዳት አእምሮንና ልብን መክፈትን ይጠይቃል፤ ፖሊቲካ ትእዛዝ ማስተላለፍን ሳይሆን መወያየትንና መከራከርን፣ ማስገደድን ሳይሆን ማግባባትን፣ ለጠቅላላው ውሳኔ፣ ለሕግና ለደንብ ተገዢ መሆንን ይጠይቃል፤ ፖሊቲካ ግልጽና ሕዝባዊ መሠረት፣ ከሌሎች ጋር የሚያቀራርብና የሚያስተማምን ቅንና መንፈሳዊ ምሰሶዎች እንዲኖሩት ያስፈልጋል፤ አንድ ደካማ ሙሴን በሆነ መንገድ ደልሎ ወይም አስገድዶ የገብርኤልን ማኅበር የሚካኤል ማድረግ ለማኅበርተኞቹ ሁሉ ብቻ ሳይሆን ለገብርኤልም ግዴለሽ መሆንንና ንቀትን የሚያሳይ ነው፤ ይህ ፖሊቲካ አይደለም፤ ቆረጣ ነው፤ መቼም ቢሆን የትጥቅ ትግል ፖሊቲካን አያስተምርም።

**ሁለተኛው አቶ ስዬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠየቅ የሚያስችለው ደረጃ ላይ አልደረሰም** ማለቱ ነው፤ ምን ማለቱ ነው? ከባድ ችግር ያለበት አባባል ነው፤ አቶ ስዬ ራሱ ይቅርታ ለመጠየቅ የሚያስችለኝ ደረጃ ላይ አልደረስሁም ቢል ይገባኛል፤ በተነገረው መንገድ ስሄድ ግን የሚገባኝ አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ጌታ በምንም ነገር ባሪያውን ይቅርታ አይጠይቅም፤ የጌታና የባሪያ ሥርዓት ባለበት ጌታ ባሪውን ይቅርታ እንዲጠይቅ የሚደረግበት መንገድ የለም፤ ባሪያ ሰው አይደለም፤ ዕቃ ነው፤ በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ውስጥ ለሴቶችም ያለው ሚዛን ወደባሪያነቱ የሚጠጋ ነው፤ ስለዚህም ሴቶችን ይቅርታ መጠየቅ የማይታሰብ ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ አቶ ስዬ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደባሪያ ቆጥሮታል ብዬ ለማሰብ አልችልም፤ ታዲያ ምን ማለቱ ነው? በእውነት ልደርስበት አልቻልሁም።

ስለይቅርታ አንድ የግንዛቤ ችግር እንዳለ ግን ይታየኛል፤ ይቅርታ ጠያቂንና ይቅርታ ተጠያቂን የሚያገናኛቸው በደል ነው፤ አንድ ይቅርታ ጠያቂ በነቢብም ይሁን በገቢር የፈጸመውን ስሕተትም ሆነ ጥፋት ለመረዳት የአእምሮ ብቃትና ትክክለኛ አስተሳሰብ የሚያስገድደው እንዲሆን ያስፈልጋል፤ የአእምሮውንና የኅሊናውን ጩኸት ለማስቀረት ራሱን ማፅዳት ይፈልግ ይሆናል፤ ይህ ካለው ስሕተቱን ወይም ጥፋቱን በአደባባይ ለመቀበልና ለማመን ደግሞ መንፈሳዊ ወኔን ይጠይቃል፤ የአእምሮ ብቃቱና መንፈሳዊ ወኔ ከሌለው ቢያጠፋም እንኳን ይቅርታ መጠየቅ ውርደት ይመስለዋል።

በይቅርታ ተጠያቂው በኩል አስፈላጊ የሚሆነው መንፈሳዊ ልዕልና ብቻ ነው፤ የደረሰበትን በደልም ይሁን ጥቃት አውቆ፣ በእርቅና በይቅርታ ክፉ ስሜትንና ቂምን ከልቡ ለመፋቅ ብቃት ያለው ሰው ወይም ሕዝብ መሆን አለበት፤ ይሁዲዎች በናዚ ጀርመን በደረሰባቸው ግፍ ካሣ የበሉ ቢሆንም ዛሬም ከስድሳ ዓመታት በኋላ በየአገሩ ማደናቸውን አልተውም፤ እኛ ግን በፋሺስት ኢጣልያ በደረሰብን ግፍ በቀቃ ካሣ ሳይሆን በቅን መንፈስ ግፋን ረስተን እየተዋለድን በፍቅር እንኖራለን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጠላትም ቢሆን የይቅር ባይነት ችሎታና ብቃት እንዳለው አስመስክሮአል፤ ታዲያ አቶ ስዬ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠብቀው ምንድን ነው? ክርክሩ ከገፋ አቶ ስዬ በእሱ ግምት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰ የሚመስለው የትኛው ሰማይ ላይ ሆኖ ነው? የሚል ጥያቄንም ያስነሣል።

በእርቅና በይቅርታ ይቅርታ ጠያቂውንና ተጠያቂውን የሚያይዛቸው የበደል ሰንሰለት ይበጠሳል፤ የሁለቱም የኅደፈ ኅሊና ይፀዳል፤ ስለዚህ ሁለቱም ተጠቃሚዎች ናቸው፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ‹‹**ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው፤**›› ያለው ለዚህ ይመስለኛል።

ከላይ ባነሣኋቸው ሁለት ቁም-ነገሮች ላይ የገለጽኋቸው ሀሳቦች የሚያመለክቱት አቶ ስዬ በአንድ በኩል የመድኅንነትን ጥሪ የተሸከመ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የጎላ ንቀት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ተመሳሳይ ባሕርይን ነው፤ በመጀመሪያው ነጥብ ላይ መድኅን ለመሆን የታሰበው ለአንድነት ፓርቲ አባሎች ሲሆን የተናቁትና የተገፉት አንድነትን የመሠረቱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ናቸው፤ በተቀነባበረ ግፊት ከአሜሪካ፣ ከብሪታንያ፣ ከጀርመንና ከሌሎች የአውሮፓ ኃይሎች መለከት እየተነፋ መድኅን መጣላችሁ ተብሎ አደራን መጠበቅ የማይችል የአንድነት አመራር ቡድን ፓርቲውን አሳልፎ ሰጠ።

በሁለተኛው ቁም-ነገርም ቢሆን በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነት ፓርቲ በኩል መድኅን ለመሆን የተፈለገው ሕዝቡን በመናቅና መንፈሳዊ ዕሴቱን በመደመሰስ ነው፤ እንዲህ በሚናቁ የፖሊቲካ አባሎች መሀል፣ እንዲህ በሚናቅ ሕዝብ መሀል ፖሊቲከኛ መምሰል ዓላማው ምንድን ነው?

ቀደም ብዬ ስለግዮን ሆቴሉ ድግስ በጻፍሁት ላይ የሚከተለውንም ብዬ ነበር፤--- ‹‹ዶር. ነጋሦና አቶ ስዬ ኤንጂኒር ግዛቸው ያቀረበላቸው መሰላል ወደላይ የሚያወጣ ይሁን ወደታች የሚያወርድ መሆኑን ሳያመዛዝኑ …›› የሚል ማሳሰቢያ ቢጤ ሰጥቼ ነበር፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መደማመጥ የማይቻልበት ባህል በመጥፋቱ አልሆነም፤ አሁን ግን የግዛቸውን መሰላል አቅጣጫ አላወቁትም ለማለት አልችልም።